# ሰሞኑን በፓልቶክ ቁጥር ሁለት
# ክህደትስ ካለነ ሙሴና አጋፋሪዎቹ ይኖራል ወይ ??

ከበልጅግ አሊ

ዘራፍ ብዬ እንድሸልል ይፈቀድልኝ እና ሰሞኑን በፓል ቶክ ብዬ በፃፍኩት ላይ የተናገርኩት እንደውስጥ አዋቂ ሰምሮልኝ የደደቦች ሸንጎ ተከፋፍሎ ሲሰዳደብ ስሰማ ከረምኩ ። የተደበቀውን ሚስጥር ከጎጃም ይሁዳነት እስከ አደገኛው ኮማንደር በጀርመንና፤ የደካማዎች የኤርትራን መንግስት ልመና፤ሁሉ ሳይቀር ሲደረደር ነው የሚያመሸው ።

„የንፁህ ኢትዮጵያውነት“ ሹመት ለዶክተር ታየ ከዛም ለኢሕአፓ በዚያውም ለህብረቱ ከልክለው ለታላቁ መሪያቸው በገፍ ሲያሸክሙ የነበሩ አጋፋሪዎች ዛሬ ደግሞ ያንኑ መሪያቸውን ልንገለው ነውና አበርራችሁ ግደሉ ወይም ይህንን ያላደረገ የሚሰጠው ስም „ቆሻሻ ኢትዮጵያዊ“ ነው ብለው ይዝቱብናል ። ለኔማ ምን ገዶኝ እንኳን ለአንድ ጎጠኛ ለታላቁ ዘረኛ ወያኔ የማልበረግግ ነኝ ።

ለነርሱ ይብላኝ እንጂ አለመሪ የቀሩት ። ለመሆኑ ክርስትያን አለክርስቶስ መሆን ይቻላል ? ኤርትራስ አለሙሴ? ይህንን ጥያቄ መጠየቅ ምን እንደሚስከትል እውቅ ነው ። በአንዲት ብጣቂ ወረቀት ከሚወዱት የከሃዲዎች መዝገብ ላይ መሰረዛቸው ያንገበገባቸው አንድ ከወደ አሜርካ የመጡ አዛውንት ትንሽ ገንዘብ ስጡኝ እንጂ እዛው ሂጄ ሙሴን ሽሬ እራሴን ሾሜ እመጣለሁ ብለው ቃል ገብተዋል ።

ገበሬው በቆሎ ሲዘራ ጦጣ ትመጣና ምንድነው የምትዘራው ?ብላ ትጠይቀዋለች ።
እሱም ሰሊጥ ይላታል።
ጦጣዋም ልናይ ሆላ አለች አሉ ።

የአጋፋሪዎቹ ሸንጎ የደረሰበትን ውድቀት ለመወጣት በኛ በኩል አስር በነርሱ በኩል ደግሞ አራት ናቸው ብሎ ሲያጣጥል ነው የከረመው በሌላው በኩል በሚሊዮን የሚቆጠር መኖሩን አጥተውተዋል ። መቼም ለኔ መሸጫውን ንገሩን ካሉኝ የምነግራቸው ቢኖር አንድ ነው የኤርትራ መንግሰት አላማ ለበለጠው አደርባይ መሸጥ ነውና እናት አገራችንን በምን ያህል እንደምትሸጥዋት አስቡበት እላችሁዋለሁ ። ሙሴ እስከጎጠንነት ስለወረደ እናንተ ደግሞ ከዛ አነስ ብላችሁ ቅረቡ ። ይህ ነው ኤርትራ ላይ የዋለው የሰሞኑ የገበያ ሁኔታ ።

ከሁሉ የሚገርመኝ ግን ይህ የደደቦች ሸንጎ ኤርትራ ውስጥ ያአሰራቸው ኢትዮጵያን እንደሉ ሲደብቀን ከርመው ዛሬ ሲጣሉ ነው የገለፁልን ። እስካሁን ድረስ አመራር አባል ነበራችሁና አላፊነትም አለባችሁ ። በሌሎች የፓልቶክ ክፍሎች በጎን ተስባስበው የሚጠብቆችሁ ሁኔታውን ዝም ብለው ያልፉዋችሁል ብዬ አለምንም ። ግለሰቦቹ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም ቦታ ጥብቅና ለመቆም ቃል የገቡ ስለሆነ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሞት አሁን የተባረራችሁትም ተጠያቂ ናችሁ ። መረጃው ከእናንት የቀረበ ስለሆነ ሙሉ ምርመራ እስከሚደረግ ድረስ ከተጠያቂነት አትድኑም ። ዛሬ ከስልጣን ወርጃለሁና አይመለከተኝም ማለት አይቻልም ። ስለሁኔታውም አላውቅም ማለትም ደግሞ አያዋጣም ብዙ „ቆሻሻ ኢትዮጵያውያን“ ስትሉ የነበራችሁዋቸው ግልፅ አውጥተው ነግረውዋችሁ እንደነበር ግልፅ ነው ።

እኔ ሂጂ ሙሴን አውርጂ ፤ ኢሳያስ በሚሰጠኝ መኪና ዘንጩ ጥሩ ዜና ይዤ እመጣለሁ የሚለውንም አንስማማም ። አንድ የምንስማማው ነገር በእናንተ የተሳሳተ ፕሮፖጋንዳ ተሳስተው ወደ ትግሉ ከመጡት ኢትዮጵያውያን መካካል ስንት የሚሆኑት በእስርቤት ፤ስንት የሚሆኑት ደግሞ በግዞት ፤ በሞት የተቀጡ እንዳሉ፤ የተብራራ መግለጫ ብቻ ነው እናንተን ከስልጣን የተባረራችሁትን ከታሪክ ነፃ ከወደፊት ፍርድም ጭምር ነፃ የሚያደርጋችሁ።አትጠርጥሩኝ ። አትጠርጥሩኝ። በሌላው ክፍል ያሉት ወጣቶች ቆሽታቸው እያረረ ነበር የከረሙት ፤ ድምፃችሁ ተቀድቶአል ሌሎች መረጃዎች ተሰብስበዋል ።

ሌላው ደግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ በየግዜው ለተጠየቃችሁት ገንዘብ የምታዋጡ ሁሉ ቢያንስ እንኳ ለዚህኛው ማዋጣት ጥቅም እንደሌው አስባችሁ የሚለውጥ ነገር ስለሌለ ሙሴንም ማንንም አልመረጠውምና አያወርደውም ብላችሁ የሰበስባችሁት ገንዘብ ወደ ሌላ ቁም ነገር ቦታ እዲውልላችሁ መጠየቅ ይኖርባችሆል ።አለበለዚያ ግን በገንዘባችሁ የምታስገድሉት ሰው መኖሩን እንድታውቁት ይገባል ።

የኔ ጥያቄ ክርስትያን ካለከርስቶስ ይኖራል ውይ ?
ክህደትስ ካለነ ሙሴና አገፋሪዎቹ ?

በልጅግ አሊ